# UNION OF TIGREANS IN NORTH AMERICA

## ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ)

P.O.BOX 73736

Washington, DC 20056

utnaoffice@gmail.com

Tel. (202) 862-4367

Fax. (202) 265-8703

www.utna.org

**ቀን፡ ኦክቶበር 03/ 2016**

**ከትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ፡**

**<u>በኢሬቻ ክብረ በዓል በደርሰው የወገኖቻችን ጉዳት ላይ የተሰጠ የሐዘን መግለጫ</u>**

በኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ ከተማ ለኢሬቻ በዓል አከባብር በወጡ ወገኖቻችን ላይ የጋጠመ እጅግ አስከፊ የሞት እና የአካል ጉዳት አደጋ የደረሰብን ስብራት እና ሐዘን ጥልቅ ነው። ለሟች ቤተሰቦች እና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን እንመኛለን። በዓሉ በሰላም ተከብሮ ሊጠናቀቅ ባለመቻሉ በተፈጠረ አለመረጋጋት፣ ንጹሐን ወገኖቻችን በአሉን ለማክበር በወጡበት መቅረታቸው በእጅጉ አስቆጥቶናል። ለአደጋው መንስኤ የኾኑትን አካላት በአፋጣኝ ተጠያቂ እንዲኾኑ ከምን ጊዜውም በላይ አጥብቀን እንሻለን። ለዚህም ማሕበራችን አቅም የፈቀደውን ሁሉ ትብብር ለማድረግ ዝግጁ እና ቁርጠኛ መኾኑን ለመግለጽ እንወዳለን። ሰላም ወዳዱ የኦሮሞ ህዝብ እንደበፊቱ የህዝብ ለህዝብ ወዳጅነቱን በማጠናከር የዚህ አይነቱን እኩይ እና የሰው ህይወት በከንቱ የቀጠፈ ተግባር ከመላው ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ በጋራ በመኾን አጥፊዎች ወደ ሕግ ቀርበው ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለማድረግ ሰከን ባለ መልኩ እንደሚሰራበት እምነታችን ጽኑ ነው። በንጹሐን ወገኖቻችን ሕልፈት የፖለቲካ ትርፍ ለመግበየት የሚሯሯጡ ከንቱ የስልጣን ጥመኞች ከምን ጊዜውም በላይ ለማውገዝ እና ለማጋላጥ ማሕበራችን ከሰላም ወዳዱ የኦሮሞ ህዝብ ጎን እንደሚሰለፍ ለመግለጽ ይወዳል።

በድጋሚ በደረሰው ግርግር ህይወታቸው ላለፉት ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን መንግስተ ሰማያት ያዋርስልን፤ እንዲሁም ለወዳጅ ዘመድ እና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን እንመኛለን!

**የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ**

**ማእከላዊ ጽሕፈት ቤት**

**ዋሽንግተን ዲሲ**